የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ—ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 6
ADDIS ABABA-6th December 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፷/፲፱፻፺፬ ዓ·ም·
ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፩ሺ፮፻፶

## CONTENTS

Proclamation No. 260/2001
OPEC Fund for International Development Loan Agreement for financing the Addis Ababa International Airport Project (Phase II) Ratification Proclamation ...... Page 1650

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፷/፲፱፻፺፬
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ አራት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (፬ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዓቀፍ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ኦክቶበር ፲ ቀን ፪ሺ፩ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፡

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ኦክቶበር ፲ ቀን ፪ሺ፩ በቪየና የተፈረመው ቁጥር ፰፻፵፭ ፐ የብድር ስምምነት ነው።

### PROCLAMATION NO. 260/2001
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of Four Million United States Dollars (USD. 4,000,000) for financing the Addis Ababa International Airport Project (Phase II), was signed in Vienna on the 10th day of October, 2001;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 6th day of December, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Addis Ababa International Airport Project (Phase II) Ratification Proclamation No.260/2001.

2. *Definition*

   In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement Number 845-P signed in Vienna on the 10th day of October, 2001 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80.001

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አራት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (፬ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of Four Million United States Dollars (USD. 4,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of December, 2001.

Done at Addis Ababa, this 6th day of December, 2001.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE